
# እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2017 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

በጁላይ የመጀመሪያው አስር ቀናት ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና በመካከለኛው እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ጥንካሬ ነበራቸው። በመሆኑም በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በምዕራብና በመካከለኛው ኦሮሚያ፣ እንዲሁም በጋምቤላ የተስፋፋ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ በመጠንም ረገድም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም የደቡብ ኦሮሚያ ደጋማ ሥፍራዎች፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሰሜናዊ ክፍል፣ የደቡብ አፋር እንዲሁም የድሬዳዋና የሀረሪ አካባቢዎች ዝናብ አግኝተዋል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል፤ በወረባቦ 116.0፣ በሾላገበያ 32.8 እና 58.7፣ በጨዋቃ 106.0፣ በአርጆ 34.2፣ በበደሌ 44.3፣ በቡለን 40.2 እና 59.7፣ በኢጃጂ 42.2፣ በኑራኤራ 44.4፣ በአርሲ ሮቤ 33.0፣ በደባርቅ 55.7፣ በጨፋ 40.1፣ በአዳማ 34.0፣ በጪራ 39.2፣ በሻውራ 42.0፣ በነቀምት 33.0፣ በሊሙገነት 35.4 እና በዝዋይ 30.0 ሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ50-250 ሚ.ሜ. የሚደርሰ ዝናብ የመካከለኛው ትግራይ፤ አብዛኛው አማራ፤ ከኦሮሚያ የምዕራብ እና ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ እንዲሁም የምስራቅና የምዕራብ ሸዋ፡ እንዲሁም አዲስ አበባ፤ ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ የመተከል የከማሺ እና የአዊ ዞኖች፤ እና ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የጉራጌ እና የሀዲያ ዞኖች ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ ከአፋር ዞን 3 እና 5፤ ከኦሮሚያ አርሲ ባሌ፣ የምስራቅና የምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም ድሬዳዋና ሐረሪ ከ5-50 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ4 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር የመካከለኛው ትግራይ፤ ከአማራ ከሰሜን ጎንደር በስተቀር ሁሉም የአማራ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ የምስራቅ ወለጋ፡ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሸዋ እንዲሁም አዲስ አበባ፤ ከአፋር ዞን 3 እና 5፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የወላይታ፣ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ አግኝተዋል(ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር







# <u>እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>
# <u>በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ</u>

በጁላይ የመጀመሪያው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች የተሻለ ጥንካሬ የነበራቸው በመሆኑ፤ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ በተለይም በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በምዕራብና በመካከለኛው ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ እንዲሁም በደቡብ ኦሮሚያ ደጋማ ስፍራዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሰሜናዊ ክፍል፣ በደቡብ አፋር እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ አካባቢዎች ጥሩ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ በመጠንም ረገድ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በጣም እርጥብ የሆነ የእርጥበት ሁኔታ ነበረዉ፡፡

ይህም ሁኔታ ክረምት ተጠቃሚ ለሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አስቀድመው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት ጥሩ ሁኔታ እንደነበረው መገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት የሚታወቁ አካባቢዎች የነበረው በጣም እርጥበታማ ሁኔታ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደርው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ጁላይ 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በአገሪቱ ምዕራባዊ አጋማሽ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የተስተዋለ ሲሆን፣ በመጠንም ረገድም በጥቂት በላይኛው ባሮአኮቦ፣ በላይኛው ኦሞጊቤ እና በአባይ ተዋሳኝ ቦታዎች እንዲሁም በላይኛው ኦሞጊቤ፣ በላይኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በአዋሽ ደቡባዊ ክፍል እና በአባይ ደቡብ ምስራቃዊ ተዋሳኝ ቦታዎች ላይ ከፍተኛ እርጥበት ተስተውላል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ አብዛኛው አባይ እና ተከዜ፣ በጥቂት የላይኛው ባሮአኮቦ፣ የላይኛው ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የላይኛው አዋሽ፣ የላይኛው ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው። በሌላ በኩል አብዛኛው የዋቢሸበሌ፣ የገናሌዳዋና የአፋርደናከል፣ የመካከለኛውና የታችኛው ባሮአኮቦ፣ የታችኛው አዋሽ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆ እንዲሁም የታችኛው ኦሞጊቤ ተፋሰሶች በአብዛኛው ክፍል ደረቅ ሁኔታ የተስተዋለ ቢሆንም በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል። በመሆኑም ባለፉት አስር ቀናት የተገኘው እርጥበት ለውሃ ፍላጎት ግብዓት አስተዋፆ ከማድረጉም በላይ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ በተከታታይ ከባድ ዝናብ በመኖሩ የወንዞች ሙላት እና በረባዳ ቦታዎች ላይ ውሃ መተኛት ተከስቷል (ካርታ 5)።

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2017 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን




## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ የሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ሥፍራዎች የሚያዳርሱበት ወይም የሚሸፍኑበት ጊዜ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ነጎድጓዳማ እና በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ዝናብ ይዘወተራል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር እያሳዩ ሊሄዱ እንደሚችሉና በአንዳንድ ቦታዎች ላይም ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ አዲስ አበባ፤ የአርሲና ቦሌ ዞኖች፤ የጋምቤላ ክልል፤ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ የትግራይ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የወላይታ እንዲሁም የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊከሰት እንደሚችል መረዳት ይቻላል። ከዚህም ሌላ ሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ፤ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ ከሶማሌ ክልል ጅግጅጋ እና ሲቲ፣ ድሬዳዋ እና ሀረሪ፤ ከአፋር ክልል ደግሞ ዞን 3 እና ዞን 5 ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ ቦታዎች በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ።

## እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

ከላይ በተሰጠው የጁላይ ሁለተኛው አስር ቀናት የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት አብዛኛዉ የሀገሪቱን የመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተስተካከለ የእርጥበት ስርጭት ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች የሚጠበቀዉ የእርጥበት ሁኔታ በተለይም የመኸር አብቃይ አከባቢዎች የዘር ወቅት እንደመሆኑ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ስለሆነ፤ ከወድሁ አስፈላጊዉን ቅድመ ዝግጅት ማድረጉ ተገቢ መሆኑን እንጠቁማለን፡፡ አስቀድሞ የተሻለ እርጥበት በነበራቸውና የጥራጥሬ ሰብሎች ዘር መዝራት በተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች በመብቀል እና በተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች እንዲሁም በበልግ ወቅት ተዘርቶ በከፍተኛ የዉሃ ፍላጎት

የዕድገት ደረጃ ላይ ለሆኑት የረጅም ጊዜ ሰብሎች የሚጠበቀው እርጥበት የተሻለ የውኃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ለሰብሎቹ ጤናማ እድገት መልካም ሁኔታን እንደሚፈጥር ይገመታል፡፡

በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀዉ ከባድ ዝናብ በተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች በማሣ ላይ ዉሃ የመተኛት ችግር እንዳይከሰት እንዲሁም ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊኖር ስለሚችል በማሣ ላይ ዉሃ የመተኛት ችግርን ለመቀነስ ተጨማሪ ዉሃ ወደ ማሣ እንደይገባ ቦይ መቅደድና ዉሃዉን የማንጣፈፍ ሥራ መሰራት ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸዉ የሚጠበቅባቸዉ አካባቢዎች መደበኛ የግብርና ሥራ ዕንቅስቃሴ ማድረጉ ተገቢ ቢሆንም፤ በአንደንድ አካባቢዎች በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ አጠር በሆኑ ቦታዎች ላይ የዕርጥበት ዕጥረት ሊከሰት ስለሚችል የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም ይኖርባቻዋል፡፡ እንዲሁም የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚኖርባቸዉ የመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በወቅቱ የግብርና ሥራ ዕንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረዉ ስለሚችል የሚገኘዉን ዕርጥበት የመቆጠብ ሥራዎችን መሥራት ተገቢ መሆኑን እንጠቁማለን ።

## እ. ኤ. አ ከጁላይ 11-20/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

የክረምቱ ዝናብ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከቀዳሚው አሥር ቀናት በተሻለ ሁኔታ በመጠናከር የክረምት ዝናብ በሚያገኙት ተፋሰሶች ላይ ቀጣይነት እንዳለው ትንበያው ያመለክታል።

ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው የአባይ፣ የተከዜ፣ የባሮአኮቦ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ የመካከለኛውና የላይኛው ስምጥሸለቆ እንዲሁም የላይኛው ገናሌዳዋና የላይኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ በእነዚህ ተፋሰሶች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ትንበያው ይጠቁማል። በተጨማሪም የላይኛውና የመካከለኛው አፋርደናከል፣ የታችኛው አዋሽ እንዲሁም የታችኛው ኦሞጊቤ ተፋሰሶች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተቀሩት ጥቂት ተፋሰሶች ላይ ከፊል ደረቅና ደረቅ ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ። በሌላ በኩል ዝናብ በሚያገኙት ተፋሰሶች ላይ ለውሃ ሃብት መጠን መጨመር ጥሩ አስተዋፆ ቢኖረውም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚከሰተው ከባድ ዝናብ

**በገደላማ ቦታዎች ላይ መሬት መንሸራተትና እንዲሁም የወንዞች ሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች ላይ ደግሞ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊስከትል ስለሚችል ጥንቃቅ ማድረግ አስፈላጊ ነው።**